የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 64
ADDIS ABABA 23rd May 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፵/፪ሺ፫

የጅማ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................ገፅ ፭ሺ፰፻፸፬

## CONTENTS

Regulation No. 240/2011

Jimma University Re-establishment Council of Ministers Regulation........................ Page 5874

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵/፪ሺ፫

### ጅማ ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የጅማ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል፡፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 240/2011

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE JIMMA UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Jimma University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 240/2011".

**2. Establishment**

1/ The Jimma University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

ያንዱ ዋጋ Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፫. **<u>ዋና ግቢ</u>**

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ጅማ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬. **<u>የተሻረ ደንብ</u>**

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፫/፲፱፻፺፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፭. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**



3. **<u>Main Campus</u>**

The University shall have its main campus at Jimma and may establish elsewhere other academic units and centres of research and community services.

4. **<u>Repealed Regulation</u>**

The Jimma University Establishment Council of Ministers Regulation No. 63/1999 is hereby repealed.

5. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of May, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**